# ይደገም..!!!!

ነጋሪተ-ድምፅ አንደምታ - የሕዝብ ባህል ጨዋታ።

የማውረድ ጥበብ ቃል - የሰው ልጅ ድምጽ ቃና፤

ነቢበ አውደ'መልዕክት - በጊዜና ቦታ፣

ሠርካች አንዘፋፊ - ደም የለው ወይ ሥጋ

ደራርቦ ማራኪ - እንበለ መሣሪያ።

ይደገም ....!!!

ነጋሪተ-ድምፅ አንደምታ - ሕዝባዊ ባህል ጨዋታ።

የማውረድ ጥበብ ቃል - የሰው ልጅ ድምጽ ቃና፤

ነቢበ አውደ'መልዕክት - በጊዜና ቦታ፣

ሠርካች አንዘፋፊ - ደም የለው ወይ ሥጋ

ደራርቦ ማራኪ - እንበለ መሣሪያ።

ገለል በል አዝማሪ - አታሞ መች ወግድ፣

አጋፋሪው አውራጅ - ይበቃሃል ሱጥ በል፣

ዳንኪራ መች እረፍ - ቁጭ በል አታሽብሽብ፣

ባረመመ ድምጹ - ይቀኝበት ሕዝብ።

መልከመልካም ልጅ ነህ - ምነዋ ማፈርህ፣

እስቲ አንገትህ ይታይ - ቀና በል ከፊትህ፣

ደረትህን ይዩት - የሴት ወይዛዝርት፤

ይማረኩ ባንተ - አሳይ ወንድነት፣

እጥፍ ዘርጋ በላ - ይመልከቱ ምት።

አንቺም የኛ ደማም...

ዐይንሽ ጀግና ይግረፍ - ነቅንቂው ዳሌሽን

እያንጉዋለልሽ ለይው - የወንድ ግርዱን ምርቱን፣

ቢነገር ቢወገር - ነገር ማይገባውን፤

ማደር መልከስከሱ - ክብር ሚመስለውን፣

እንዝልል ለማጁን - ሱሪ ማይወደውን፣

ፊትሽን አዙሪበት - ይረዳው ንቀትሽን፣

እንኩርፊያውን ያቁም - ንገሪው እንቅልፉን፣

ይንቃ ወጦ ይግባ - ከወደደሽ አንችን።

ቢ ......ስ! ...ይደገም!!

እስቲ አንገትህ ይታይ - ቀና በል ከፊትህ፣

ደረትህን ይዩት - የሴት ወይዛዝርት፤

ይማረኩ ባንተ - አሳይ ወንድነት፣

እጥፍ ዘርጋ በላ - ይመልከቱ ምት።

አንቺም የኛ ደማም...

ዐይሽ ጀግና ይግረፍ - ነቅንቂው ዳሌሽን

እያንጉዋለልሽ ለይው - የወንድ ግርዱን ምርቱን፣

ቢነገር ቢወገር - ነገር ማይገባውን፤

ማደር መልከስከሱ - ክብር ሚመስለውን፣

እንዝልል ለማጁን - ሱሪ ማይወደውን።

እንዲህ ነች ጨዋታ - በአንገት በደረት፣

በድምጽ እንጉርጉሮ- በዐይን ወግቶ ማየት

ትክሻ መነቅነቅ - አርገፍግፎ ማውለቅ።

ይደገም .... ቢ ....ስ!

እንዲህ ነች ጨዋታ - በአንገት በደረት፣

በድምጽ እንጉርጉሮ- በዐይን ወግቶ ማየት

ትክሻ መነቅነቅ - አርገፍግፎ ማውለቅ።

ሁሉም አጉረምራሚ - በድምጹ ማት አውራጅ

ቀን እየጠበቀ - እያሰላ ስንኝ፣

ግንቦት ላይ ደርድሩዋል - የየካቲት ተቀኝ!!

ጨዋታው ብሂሉ - ዜማው እንዲህ ይላል፣

ማን ይመርጣል መዥገር - ማን ይወዳል ጅል፣

ማን ያፈቅራል ጠላት - ሌባን ማን ያከብራል -

ይጋለጣል እንጅ -ይጣላል ይወድቃል።

ይደገም...!!

የየካቲት ዜማ - ግንቦት እንዲህ ይላል..

ማን ይመርጣል መጥፎን - ማን ያሻዋል ጅል፣

ማን ይወዳል ጠላት - ሌባን ማን ያከብራል -

ይጋለጣል እንጅ -ይጣላል ይወድቃል።

.............////////////////.........

ረታ ታከለ

ተጣፈ

ግንቦት 2002